# ገድለ ልደቱ (ከህደቱ )

በልጅግ አሊ

-፩-

እነሆ የከሃዲዎች አጸያፊ ምግባር ይፃፍ ዘንድ ቃል ተገብቷልና ቃሉ ይፈፀም ዘንድ ተጀመረ።

የወያኔ መልዕክተኛ ብላቴናውን ልደቱን (ከህደቱን) ቀረበው ። እንዲህም አለው ፡ -

"ወዳጄ ልጄ የወገቤ ክፋይ ! በችግሬ ጊዜ ወደ አንተ እንድመጣ ቃል ገብተህልኛልና ወደ አንተ መጣሁ። አሁንም ቃልህን ትጠብቃለህ ወይ ? " ብሎ ጠየቀው ።

"ፈጣሪዬ ወያኔ ሆይ ! ካለ አንተ ማን አለኝና እንቢ ልበልህ? አንተም እንደምታውቀው ሕዝብ በእኔ ላይ አድመው መቆሚያ መቀመጫ አሳጥተውኛል። በውጭ የሚገኙ ተቃዋሚዎችም ቁም ስቅሌን አሳይተውኛል። ሥራዬን ለሕዝብ እያጋለጡ መድረሻ አሳጥተውኛል። ሆኖም ሊጥ ውስጥ እንደገባች ውሻ ቢያዋከቡኝም የአንተን ቃል እፈጽማለሁ። እዘዘኝ" ብሎ መለሰ።

የወያኔውም ተወካይ እንዲህ አለው ፡ -

"እነሆ ለሁሉታችንም ችግር መፍትሄ የሚሆነውን ይዤ ወደ አንተ መጣሁ ። እንደምታውቀው የሕዝብ ፍቅር እንድታገኝ፣እንደ ተቃዋሚም እንድትቆጠር በተስማማነው መሠረት ፓርላማ እንዳትገባ አድርገን ነበር።ፓርላማ ስላልገባህ እንደ ተቀዋሚ ስለተቆጠርክ ያገኘውን "የሕዝብ ፍቅር" መፈተሻው ጊዜ ደርሷል ። የአውሮፕላን ትኬትህና አሜሪካና እንግሊዝ የሚያስገባህ ቪዛ ይዘጋጅልሃል ። ሂድና ተቃዋሚዎቻችንን ፈትሻቸው። መንገዱ ሙሉ በሙሉ ጥሩ ላይሆን ይችላል። ይህንን የምነግርህ በደጋፊዎቼ ላይ ፈተና እንደሚበዛባቸው ስለማውቅ ነው ።በተለይ በውጭ ሃገር አጋዚም ስለሌለ ፣ ማሰርም ፣መግረፍም ስለማንችል ተቃዋሚዎቹ እንደ ሃገር ቤቱ  ቀላል እንዳይመስሉህ ። ትንሽ ሊያስቸግሩህ ይችላሉ። ነገር ግን የተከፋፈሉ ስለሆኑ አንድ ሆነው አይቃወሙህም፤ በውስጣቸውም የኛ ሠርጎ ገቦች ሰላሉ እንዳትፈራ ።አሁን በበለጠ  የሚከፋፍላቸውንም መንገድ ሁሉ ተጠቀም። በዓለም የተበተኑ ደጋፌዎቻችን አንተን ይረዱ ዘንድ ታዘዋል ። ሂድና አስተምር ።" ብሎ ወደ አሜሪካና አውሮፓ ላከው።

ልደቱ ከህደቱም ፡ -

"ጌታዬ ወያኔ ሆይ! እነሆ በተስማማነው መሠረት ከፓርላማ ከወጣሁ በኋላ በሕዝብ በኩል ትንሽ የመሻሻል ሁኔታ ይታያል።ብዙዎቹ ከፖለቲካ የተወገድኩ ስለመሰላቸው ተወት አድርገውኛል።በውጭ ሀገር ያሉትን ተቃዋሚዎች መከፋፈል ቅድሚያ ሥራችን መሆኑን ልንዘጋው አይገባም። በዚህ ሥራችን ለአንተም እረፍት ለእኔም ደግሞ ወደ ፖለቲካው ሊመልሰኝ ስለሚችል ሃሳብህን ተቀብያለሁ ።ተግባራዊም አደርጋለሁ። የምለምንህ ነገር ቢኖር  ደጋፊዎችህና አባሎችህ ከጎኔ እንዲቆሙ እዘዝልኝ ። የገንዘብ ችግርም እንዳይኖርብኝ ኤምባሲዎች ይታዘዙልኝ ። "

የወያኔ ተወካይም እንዲህ አለው ።

ይሄ ለግል ጥቅሙ ያደረ ፣ ከህደት የተሞላ ያለውን እንደሚፈጽም በመተማመን በፈገግታ "አይዞህ!በሰሜን አሜሪካ አምባሳደራችን ተነግሮታል። የገንዘብ ችግር በፍፁም አይኖርብህም። በዛ ሃገር ያሉ ደጋፊዎቻችንን ለአንተ ቆመው፣ አንተን መስለው ይታገሉ ዘንድ ታዘዋል፡፡ ራዲዮኖቻችንና ድረ ገጾቻችን ስላንተ ያወድሳሉ። ጥርጥር እንዲገባህ አያስፈልግም ። በሰሜን አሜሪካ ብርሃኑንና ኢሕአፓን መሳደብህን እንዳትረሳ ።እንደ ሁኔታው አቋምህን ቀያይር። የኢሕአፓ ተቃዋሚዎች በሚበዙበት ቦታ ኢሕአፓን ስደብ ፣ የግንቦት ሰባት ተቃዋሚዎች ከበዙ ብርሃኑን ስደብ ፣ የሰላማዊ ትግል ደጋፊዎች ከበዙ የመሣሪያን ትግል አውግዝ። እንደየሁኔታው በየሃገሩ ከሚገኙ በዚህ ሥራ ላይ ከተመደቡ ሰላዮቻችን መመሪያ ይደርስሃል"። ብሎ መመሪያ ሰጠው ::

በሰሜን አሜሪካ ብላቴናው የተባለውን ፈፀመ :: በሬዲዮ ቀርቦ ፖተለከ። አቅራራ። የወያኔን የሞት ፍርድ አስፈፃሚ ሆኖ ቀረበ። በወያኔ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ግለሰብ ፍርዱ እንቅልፍ እንደሚነሳው አበሰረ ። ሕዝብ ግን ጠየቁ እውን በውጭ ያለ ግለሰብ በሞት ፍርድ ምክንያት እንቅልፍ የሚነሳው ከሆነ ለዘመናት  በወያኔ ጉድጓድ እስር ቤት ውስጥ የታሰሩ እነ ጸጋዬ ደብተራው እንዴት ዓይነት ኑሮ ይገፉ? 20000 በላይ የሆኑት ያለ ፍርድ የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞችስ እንዴት ይሆኑ ? በግፍ የተገደሉትስ  እንዴት ይሁኑ ? የወያኔ ፍርድ የተዛባ መሆኑን ከህደቱ እንዳልገባው ፣ እሱንም በውጭ ሃገር ማስፈፀም እንደማይችልና ፣ የፖለቲካ ጨቅላነቱን ፣ የፖለቲካ ድህነቱን አይተው ሕዝብ ተዘባበቱበት።

ብላቴናው በሰሜን አሜሪካ ሥራውን ፈጽሞ ወደ እንግሊዝ እንዲሄድ ታዘዘ ፡ -

"በለንድን ጠንከር ያለ ደጋፊ ስለሚኖረን እንድትሄድ ።ለንደን በጣም ያስፈልገናል።በቅርቡ የአማራ ስብሰባ ጠርተናል ። ምን ያህል እንደሚሳካልን መፈተን እንፈልጋለን ። የአንተን ሁኔታ አይተን የምናደርገውን ጥንቃቄ ስለምናስተካከል ሂድና ሞክራቸው። ተጋድሎህንም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ሠራተኞቻችን እየተከታተሉ ይቀርፁልሃል" ።

ይህንን የወያኔን ሤራ በሰሙ ወቅት በእንግሊዝ የሚገኙ ዜጎች በውስጣቸው ያለውን ልዩነት አቻችለው ተነሱ ። ውስጥ ለውስጥም ተነጋገረው ጨረሱ። የጋራ ጠላታችን ወያኔ ነው ብለው ተስማሙ ። ሁሉም በጋራ ተነስተው ጠላታችን አንተ ነህ ብለው ክህደቱን ፈረጁት ። ይዞት የመጣውን የመከፋፈል እፀ በለስ አንበላም አሉት ።ብላቴናው በለንደን የውርደት ሸማውን ለበሰ። የወያኔም ድረ ገጾች ተሸማቀቁ ። ተከታዮቹ አሁንም በየቦታው የወያኔን ፍርፋሪ ለመቅመስ ሲሉ እንደ ተራብ ውሻ እየጮኹ ናቸው። በተለይ በለንደን የተሰበሰቡት ደጋፊዎቹ በዚህ ዝግጅት እናተርፋለን ፣ ከወያኔም ጥቅም እናገኛለን ብለው እየተሯሯጡ ናቸው ።

**እነሆ በዚህ መንገድ የሚገኝ ንዋይ የዘላለም ጸጸትን ያመጣልና አሕዛብ ይጠንቀቁ ።**

እነሆ በቅርብ ቀን በለንደን አሕዛብን ለመከፋፈል ወያኔ "አማራ" በማለት ስብሰባ ተጠርቷል።ይህ የዘረኞችን ከፋፋይ ጥሪ ለማከሸፍ አሕዛብ በአንድነት ቆመዋል ። ከደርጅት ጎጆ ባሻገር ይህንን ሰይጣናዊ ከፋፋይ ምግባር ለማምከን ተሰብሰበዋል ።አዋጅም እየተነገረ ነው ።

**እነሆ ወያኔ የመጨረሻውን ጉዞ ጀምሯል። ትንቢትም እየተነገረ ነው። መጀመሪያ "አማራ" በሚል ይሰበሰብባል።ቀጥሎም "ኦሮሞ" ብሎ ይጠራል። ከዛም ሁላችንንም በዘር ፣ በጎሳ ይመድባል ። በውጭ ያለውን ተቃውሞ ለማምከን አሕዛብን በዘር ለመከፋፈል ጥረት ላይ ነውና ።**

**የአሕዛብ ዘር ሁሉ ተሰባሰብ !**
**ሃገርህን የምትወድ ተሰባሰብ !**
**በዘር መከፋፈል የለብንም የምትል ተሰባሰብ !**

ለንደን ላይ ይህንን ተግባር በእንጭጩ ካላከሸፍን፣ ሊራባ ይችላልና አሕዛብ ጥሪውን ስማ ። ሆዳሞች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ረግጠው ወደዚህ ከፋፋዮች ድግስ ይገቡ ዘንድ ሊፈፀም ነውና ነቃ ብለህ ጠብቅ ። በዚህ ድግስ የሚሳተፉ ሆዳሞች፣ አድርባዮች ከሕዝብ በግፍ የተሰበሰበው ንዋይ በድግስ ስም ሊቃደሱ እየተሽቀዳደሙ ነው ።

በዚህ ድግስ በመሳተፍ የሚጠጡት መጠጥ በኢትዮጵያ ውስጥ በወያኔ የተገደሉ ንፁሃን ዜጎች ደም ነው ። የሚበሉትም የሰማዕታቱን ሥጋ መሆኑን ያውቁት ዘንድ ይነገር ። የልደቱ ደጋፊዎችም ከዚህ አሣፋሪ ምግባር እጃቸው ካላነፁ በተሰውት ሰማዕታት ደም እየታጠቡ መሆኑን ያውቁት ዘንድ በግልጽ ይነገር ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆኑ ድርጅቶች ውጭ ሃገር ያለው ኢትዮጵያዊ በዘር መከፋፈል አደገኛ መሆኑን ያስረዱ ዘንድ ይተባበሩ ።

እነሆ የኢትዮጵያውያን ድረ ገጾች፣ ራዲዮኖች ፣ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሁሉ ይህንን እኩይ ተግባር ያጋልጡ ዘንድ በአንድነት ይቁሙ ።

beljig.ali@gmail.com

ተነስ ! ተነስ ! ተነስ !

ስለ ኢትዮጵያ አንድነት የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም ! ! !

ኅዳር 2003 - ሎንዶን